# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 60 ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ለወያኔ ትንኮሳ የደሴ ሞስሊም ማኅበረሰብ በሰጠው «እኛ ተቃውመን አናውቅም ምላሽ» ወያኔ ምን ያህል እንዳፈረ መገመት ቀላል ነው:: እንዲህ ዓይነት ዓይን ያወጡ ትንኮሳዎች በደሴም በሌሎችም ቦታዎችም መቀጠላቸው አይቀርም ምላሻችን እንደ ደሴ ሞስሊም ወንድሞቻችን «አንጣላልህም፤ ይልቁንስ የችግሮቻችን ምንጭ አንተ ነህና ወጊድ!» የሚል መሆን ይኖርበታል::

**ርዕስ አንድቀጽ**

የሚሄድበትን የሚያውቅና ወጥ አመራር ያለው፤ እዚያም እንዴት እንደሚደርስ በደንብ ያሰበበትና እዚያ ለመድረስ በሚያስፈልገው እስትራቴጂም ላይ ሙሉ ስምምነት ያለው ትብብር

**ዶር ብርሃኑ ነጋ**

## በዘር ፍጅት የተከሰሰው ዘረኛው መለስ ዜናዊ የዘር ፍጅትን በማስቆም ተሸለመ

አለም አቀፍ ከበሬታ እና ተደማጭነት ባለቸው የሰብአዊ መብት እና የዘር ፍጅት ተከላካይ ተቋማት በሰብአዊ ፍጡር ላይ ወንጀል በመስራት እና በዘር ፍጅት የተከሰሰው ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ፤ ከአስራ አምስት አመት በፊት በሩዋንዳ የተካሄደውን የዘረ ፍጅት ለማቆም ከፍተኛ ሚና ከተጫወቱት አንዱ ነው ተብሎ መሸለሙ የአፍሪካ መሪዎች ስለ ሰብአዊ መብት እና ስለ ዴሞክራሲ ያላቸውን ደካማ አስተሳሰብ ያጋለጠ ተጨማሪ አብነት መሆኑ ተገለጸ። ባለፈው በተከበረው የሩዋንዳ ብሄራዊ የነጻነት ቀን ለመለስ ዜናዊ የሀገሪቱን የክብር ሜዳሊያ የሰጠው በጸረ ነጻ ፕሬስ አቋሙ እና የፓለቲካ ባላንጣዎቹን አሳዶ በመምታት የሚታወቀው የሩዋንዳው ፕሬዝደንት ፓውል ካጋሜ እንደሆነ ታውቋል።

ከዚህም ባሻገር መለስ ዜናዊ የዘር ፍጅትን አስከፊነት የሚያሳይ ዘመቻ በማድረጉ ተጨማሪ ሽልማት እንደሚሰጠው ተገልጿል። የፓውል ካጋሜ መንግስት ለመለስ ዜናዊ ሽልማቱን ለመስጠት የፈለገለው እንደተባለው የሁቱ ኢንተርሀውሜ ሚሊሻ ከስምንት መቶ ሺህ በላይ ቱትሲ እና ለዘበተኛ ሁቱዎችን የፈጀበትን አሰቃቂ ጭፍጨፋ ለማስቆም ሚና ስለተጫወተ ሳይሆን

**(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## የወያኔው አገዛዝ በአለም ላይ ካሉ 10 አፋኝ፣ ገዳይና አሸባሪ መንግስታት መካከል አንዱ መሆኑን አንድ ታዋቂ አለም አቀፍ ድርጅት አጋለጠ

ማይኖሪቲ ራይትስ ግሩፕ ኢንተርናሽናል የተባለ ታዋቂ አለማቀፍ ድርጅት በሀምሌ 2009 ሪፓርቱ በዘር ማጥፋት፣ በጅምላ ግድያና በአጠቃላይ ከባድ የሆኑ ሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በመፈጸም ተወዳዳሪ የሌላቸው አገሮች ብሎ ከዘረዘራቸው መካከል ኢትዮጵያ በቀዳሚነት ከተጠቀሱት 10 አገሮች ውስጥ ተመድባለች።

ህዝቦቻቸው በከፍተኛ ስጋትና አደጋ ውስጥ ከሚገኙ አገሮች ተብለው ከተጠቀሱት ውስጥ ዋናዋናዎቹ ሶማሊያ፣ ኢራቅ፣ሱዳን፣ አፍጋኒስታን፣ በርማ፣ ኮንጎና ኢትዮጵያ ሲሆኑ ፣ በ2009 ከፍተኛ የሆነ፣ የዘር ማጥፋት፣ የጅምላ ግድያና የሰብአዊ መብት ጥሰት ከፈጸሙ አገሮች ማካከል ፓኪስታንና ኢትዮጵያ በጋራ አንደኛ ሆነው ተመርጠዋል።

በሪፖርቱ ወያኔ በሶማሊያ፣ አፋር፣ አኙዋክና በሌሎችም አናሳ ህዝቦች ላይ እጅግ ከባድ የሆነ ግፍ መፈፀሙ ተዘግቧል።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በድህው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ከቀን ወደ ቀን የሚፈጽመው አሰቃቂ ግፍ በአለማቀፍ ድርጅቶች እየተወገዘ እንደሚገኝ የሚታወቅ ሲሆን፣ ሰሞኑን በማይኖሪቲ ራይትስ ኢንተርናሽናል የወጣው ሪፖርትም እስካሁን ድርስ የወጡትን ሪፖርቶች የሚያጠናክርና ዘረኛውን መለስ ዜናዊና ግብራበሮቹን ባለማቀፍ የወንጀል ማስቻያ ፍርድቤት አቅርቦ ለማስዳኘት ተጨማሪ ማስረጃ እንደሚሆን ታምኖበታል።

ግፈኛው መለስ ዜናዊ፣ ለብሄሮች እኩልነት ቆሜያለሁ እያለ፣ በተግባር ግን የሚፈጽመው እነዚህን ብሄሮች የማጥፋት ስራ እንደሆነ በሶማሊያ፣ ጋምቤላ፣ አፋርና ሌሎችም ቦታዎች የሚፈጸሙ ድርጊቶች ያመለክታሉ።

ሂዩማን ራይትስ ወችና ጄኖሳይድ ወች የተባሉ ድርጅቶች ዘረኛውንና አምባገነኑን መለስ ዜናዊና ግብራበሮቹን በጦር ወንጀልና በሰው ልጆች ላይ በፈጸሙት የጅምላ ግድያና የዘር ማጽዳት ስራ በአለማቀፍ የወንጀል አስቻይ ፍርድቤት እንዲቀርቡ ግፊት በማድረግ ላይ መሆናቸው ይታወሳል። የዘረኛው መለስ አገዛዝ የሚፈጽማቸው በደሎች ከቀን ወደ ቀን እየጨመሩ መምጣታቸው፣ አገዛዙ የኢትዮጵያን ህዝብ በሀይል ካልሆነ በፍቅር ማስተዳደር በማይችልበት ደረጃ ላይ መገኘቱን ያመለክታል።

**(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## የኢትዮጵያ ህዝብ ግንቦት 7 እያቀረበ ላለው ሁለገብ የድጋፍ ጥሪ የሚሰጠው ምላሽ አስደናቂ መሆኑ ተነገረ።

በውጭ አገርና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ግንቦት 7ትን የኢትዮጵያን ትንሳኤ አምጭ ሀይል አድርገው በመቁጠር፣ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ፣ የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ላይ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ በየቀኑ በሽዎች የሚቆጠሩ የአባልነት ማመልከቻዎች በመቅረብ ላይ ሲሆኑ፣ ንቅናቄውም በተቻለው ፍጥነት ሁሉ ሰዎችን በተገቢው ቦታ በበመደብ ላይ ይገኛል። ከአባልነት በተጨማሪ በገንዘብ፣ በቁሳቁስና በሞራል የሚሰጠው ድጋፍም በሚያስገርም ሁኔታ እየቀጠለ መሆኑ ታውቋል። **(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

## መለስ አገዛዝ የምሥራቅ አፍሪካ መረጋጋት ዋነኛ እንቅፋት መሆኑን አለም እየተረዳ መጥቷል

የኢትዮጵያ ጦር ዳግም ወደ ሶማሊያ የመመለሱን አላስፈላጊነት አስመልክቶ በአሜሪካ የውጭጉዳይ መስሪያ ቤት የ አፍሪካ ክፍል ሀላፊ ሰሞኑን የሰጡት መግለጫ -ለመለስ ዜናዊ ፖለቲካ ከፍ ያለ ኪሳራ ነው ይላሉ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ ምሁር ።

ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉት እኚሁ ምሁር ከግንቦት ሰባት ዘጋቢ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ፡-የአፍሪካ ጉዳይ ሀላፊው ጆን ካርሶን- ኢትዮጵያ ዳግም ወደ ሶማሊያ መግባቷ ለአገራቸው ለአሜሪካም ሆነ ለራሷ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ስላልሆነ የሽግግር መንግስቱን ለመርዳት በሚል ምክንያት ጦሯን እንዳትልክ ማሣሰባቸው መለስ ዜናዊ ከሚጠብቀው አስተያዬት 380 ዲግሪ ያህል በተቃራኒው የዞረ ነው ብለዋል።

ባለፈው ጊዜ የአገር ውስጥ ፖለቲካዊ ቀውሱን አቅጣጫ ለማሳትና “የጌቶችን ጥቅም በማስጠበቅ ቡራኬና ፍርፋሪ መቃረም “ በሚል ስሌት ግራና ቀኙን ሳይመለከት እሳት መሀል ዘው ብሎ የገባው የመለስ ቡድን በዚህም የደመ-ነፍስ እርምጃው በዓለማቀፍ ዕውቅ የሰብ ዐዊ መብት ተሟጋቾች ዘንድ በጦር ወንጀለኝነትና በሰው ልጆች ህይወት ላይ በተፈፀመ ዘግናኝ ወንጀል ሊወራረድ የማይችል ከባድ ክስ እንደተመሰረተበት ይታወሳል።

እንደ ምሁሩ ገለፃ በጣም አስገራሚው ነገር መለስ ዜናዊ ከሀያላን ጋር ወዳጅነቴን አጠብቅበታለሁ በሚል ስሌት ከገባበት ጦርነት ኢኮኖሚያዊና ሰብዓዊ ኪሳራ፣ እንዲሁም ውግዘትና ክስ ማትረፉ ብቻ ሳይሆን- የተፈፀመውን የጦር ወንጀል በምስል አስደግፈው ለዓለማቀፍ ተቋማቱ ያጋለጡት የአሜሪካ የሳይንቲስቶች ቡድን አባላት ጭምር መሆናቸው ነው።

ሁኔታው አስደንጋጭ የሆነበት የመለስ ቡድን ከሶማሊያ እግሬ አውጭኝ ሲል- በዓለማቀፉ ማህበረሰብ በተለይም በተባበሩት መንግስታትና በሀያላን አገራት ላይ “ሊረዱን አልቻሉም” በሚል ምክንያት የበረታ እሮሮና ወቀሳ ማሰማቱን ምሁሩ ያስታውሳሉ።

እንደ ምሁሩ አስተያዬት ከሮሮው በስተጀርባ ያሉት ዋነኛ መልዕክቶች “እኛ የናንተን ጥቅም ለማስጠበቅ ጦርነት ውስጥ ገብተን -ያሰላነውን ያህል እርዳታ አልሰጣችሁንም፤ ይባስ ብሎ እኛ ለእናንተ ስንል እሳት ውስጥ ተማግደን ለክስ አሳልፋችሁ ሰጣችሁን” የሚሉ ናቸው-።

ለዚህም ሰሞኑን መለስ አዲስ አበባ ላይ ለአገር ውስጥ ጋዜጠኞች የሰጠውን መግለጫ ማጤን በቂ ነው ባይ ናቸው-ምሁሩ። “የሽግግር መንግስቱ ለጎረቤት አገሮች በ 24 ሰዐት ውስጥ የድረሱልኝ ጥሪ ስላቀረበ ኢትዮጵያ ጦሯን ትልካለች ወይ ?” ተብሎ የተጠየቀው መለስ፤ “ አለማቀፉ ማህበረሰብ በግልፅ ማረጋገጫ እስካልሰጠን ድረስ እንደባለፈው ጊዜ ተንደርድረን አንገባም” ማለቱን የጠቀሱት ምሁሩ “ይህ መልስ በአንድ በኩል የመለስ ቡድን በአካባቢው ለተፈጠረው ችግር ያለ እሱ መፍትሄ የሚሆን ሀይል እንደሌለ በመቁጠር በዐለማቀፉ ማህበረሰብ ላይ ሊኩራራ መሞከሩን ፤በሌላ በኩል ደግሞ በነሂዩማን ራይትስ ዎችና በነ አምነስቲ ኢንተርናሽናል በቀረበበት የጦር ወንጀለኝነት ክስ ክፉኛ መደንገጡን የሚያሳይ ነው ይላሉ።

መለስ ይህን መግለጫ የሰጠው ዓለማቀፉ ማህበረሰብ ለሶማሊያ ችግር ከኛ የተሻለ አጋር ሊያገኝ አይችልም ከሚል በአየር ላይ ከተንጠለጠለ ባዶ ግምት እና ከጦር ወንጀለኝነቱ ክስ ፍራቻ ለመሆኑ ቅንጣት ሚያጠራጥር አይደለም ያሉት ምሁሩ፤ ሆኖም በመጠኑም ቢሆን የወንጀል ዕዳውን ለማቅለል ሊጠቀምበት የጓጓለት ይህ አጋጣሚ በአሜሪካ መንግስት ያልተጠበቀ መግለጫ ጆሮን ጭው የሚያደርግ መርዶ ትቶለት አልፏል ብለዋል።

**(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)**

**በሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች የኅብረት ትግል ወያኔን ለማስወገድ ቆርጠን እንነሳ**

ሰሞኑን በደሴ ከተማ ወገኖቻችን ላይ የደረሰው አሰቃቂ ጭፍጨፋ፣ የአካል ጉዳትና ሽብር ከዚህ ቀደም *«የመለስ ዜናዊን የአጥፍተህ ጥፋ ሴራ ማምከን የሁሉም ኢትዮጵያዊ የዜግነት ግዴታ ነው»* በሚል ርዕስ በቁጥር 49 ጋዜጣችን ርዕሰ አንቀጽ፣ በሌሎች በርካታ የግንቦት ሰባት ጽሁፎች እና የጉባዬ ውይይቶች አንስተነው ወደነበረው ወያኔ በሃይማኖት ሰበብ በሕዝባችና አገራችን ላይ ስለሚያደርሰው በደል እንደገና እንድንመለስበት አድርጎናል።

ከሁሉ አስቀድመን በአረመኔው የወያኔ ጥይት ውድ ሕይታወቻቸው ላጡ ወገኖቻችን የተሰማንን ጥልቅ ሃዘን እየገለፅን ለቤተሰቦቻቸውና ለሁለቱም ሃይማኖቶች ምዕመናን መጽናናትን እንመኛለን። እንደዚሁም ለተለያዩ የአካል ጉዳቶች እና ሰቆቃዎች ለተዳረጋችሁ ወገኖቻችን ህመማችሁ ህመማችን፤ ቁጭታችሁ ቁጭታችን መሆኑን በጥልቅ ሃዘን ስንገልጽ ይህንን ሰቆቃ የነደፉ፣ የፈቀዱና ያካሄዱ የወያኔ ሹማምንትና ሎሌዎቻቸው ለፍርድ የሚቀርቡበትን ጊዜ ለማሳጠር ጠንክረን እየሠራን መሆኑን እናረጋግጣለን።

ኢትዮጵያ ተቀራራቢ ቁጥር ያላቸው ሙስሊምና ክርስቲን ዜጎች ያሏት መሆኑን፤ ሁለቱ ሃይማኖቶች ተከባብረው ሙስሊሙ የክርስቲያኑ፣ ክርስቲያኑ ደግሞ የሙስሊሙን በዓል የሚያከብርበት አገር እንደሆነች፤ ይህ ባህል የኢትዮጵያ ክብር መሆኑ፤ ሙስሊምና ክርስቲያን ተደጋግፎ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር ከቻለ ለአፍሪቃ ቀንድ ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ትልቅ ትምህርት ሰጭ ተግባር ሊሆን እንደሚችል ግንቦት ሰባት ከላይ በተጠቀሰው ርዕሰ-አንቀጽ፣ በሌሎች ጽሁፎችና ባካሄዳቸው ጉባዬዎች በተደጋጋሚ ገልፆዓል። ወያኔ ኢትዮጵዊያንን በዘር ለመከፋፈል ሞክሮ የጠበቀውን ያህል ውጤት ባለማግኘቱ ሃይማኖትን በተጨማሪ መሣሪያነት ሊጠቀም መወሰኑን በተግባር እያሳየ መሆኑን በጅማ፤ በሃረር፣ በአዲስ አበባ እና ጎንደር የታዩትን ምልክቶች በመጠቃቀስ ተችቶባቸዋል። በሃይማኖት ሰበብ የሚነሳ ቅራኔ በዘር ሰበብ ከሚነሳ ቅራኔ የባሰ አውዳሚ እና በቀላሉ ድንበር ተሻጋሪ መሆኑን በመገንዘብ ሁላችንም ይህንን መሰሪ ተግባር ነቅተን እንድናከሽፍ ግንቦት ሰባት ጥሪ ሲያደርግ ቆይቷል።

የወያኔ ሃይማኖትን ለእኩይ ግቡ የመጠቀም መሰሪ ተግባር ደሴ መዝለቁ የጉዳዩን አሳሳቢነት አጉልቶ ያሳያል። እንደሚታወቀው ወሎ የእስልምናና ክርስትና ሃይማኖቶች ከመቻቻልም አልፎ መፋቀር የሚችሉ መሆኑን ማስመስከር የቻለች ነች። በወሎ በተለይም በደሴ ዙርያ ክርስቲያኑና ሞስሊሙን በስምም ይሁን በባህሪይ መለየት እስከማይቻል ድረስ የተቀራረቡ ናቸው። ከፊል አባላቱ ክርስቲያን፤ ከፊሉ ደግሞ ሞስሊም የሆነባቸው ቤተሰቦችን በመያዝ ደሴ ዙሪያ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከመላው ዓለም ቀዳሚ ናት። አሁን የጭፍጨፋው ሰበብ የሆነው የአርሴማ ቤተክርስቲያን ግንባታ ጉዳይ ከእስከዛሬዎቹ የወያኔ ትንኮሳዎች ሁሉ የባሰ መርዛማ ያደረገው በወሎ መደረጉና ዓይን ባወጣ መንገድ የሁለቱን ሃይማኖቶች ተከታዮች ለማጋጨት የታለመ በመሆኑ ነው።

ይህ የወያኔ አሳፋሪ የተንኮል ታሪክ ባጭሩ የሚከተለው ነው። ለደሴ አርሴማ ቤተክርስቲያን ግንባታ በተጠየቀው መሬት ላይ የከረረ የሞስሊሞች ተቃውሞ አልነበረም፤ መለስተኛ ቅሬታዎችም የሃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ከሁለት ዓመት በፊት ተነጋግረው ጨርሰውት ቤተክርስቲያኒቷም ለሁለት አመታት በዚሁ ቦታ በድኳን ውስጥ አገልግሎት ስትሰጥ ቆይታለች።

ሲያሻው መሬት በመስጠት አሽከሮቹን ሚሊነር ማድረግ፤ ጥቅማቸው ሲያበቃ ደግሞ የሰጠውን መሬት በመቀማት በቅጽበት ወደ ቀድሞ ድህነታቸው በመመለስ የተካነው ወያኔ መሬት ለመስጠትም ሆነ ለመንፈግ ምክንያት መስጠት አያሻውም። ወያኔ የአርሴማን ቤተክርስቲያን ይዞታ ለካድሬዎቹ ማደል ፈልጎ ከሆነ ይህንኑ መንገር የሚከለክለው የለም። ከፈለገም በመከረኛው «ልማት» በማሳበብ «ቦታውን ለልማት እፈልገዋለሁ» ማለት ይችል ነበር። ወያኔ የአገሪቷ መሬት ብቸኛ ባለንብረት መሆኑ ለእንዴህ ዓይነት እኩይ ተግባር እየተጠቀመበት መሆኑ አገር ያወቀው ሃቅ ነቅ። እናም ይኽ ሁሉ አማራጭ እያለ «መሬቱ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ያልተፈቀደው ሞስሊሞች ስለተቃወሙት ነው» ብሎ ማስወራት እንደምን ያለ አስነዋሪ ተግባር ነው? ለምንስ ይኸንኑ ምላሽ ለሠላማዊ ሰልፈኞቹ በኦፊሴል አልሰጠም? የከተማው አስተዳደር ተብየው ለሰላማዊ ሰልፍ ፈቃድ ሲሰጥ የሰልፈኞቹ ጥያቄ ምን ሊሆን እንደሚችል አልገመተም ነበር ይሆን?

የሰላማዊ ሰልፈኞቹ ጥያቄ ግልጽ ነበር፤ በማመልከቻቸውም በግልጽ ሰፍሯል። ምዕመናኑ ለከተማው አስተዳደር ያቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ ምላሽ በማጣቱ የተጠራ ሰልፍ ነበር። ሆኖም ሳይመረጥ የከተማው አስተዳደር ነኝ ብሎ ራሱን የሰየመው የወንበዴው አካል የሕዝብን ጥያቄ ለማስተናገድ ፈቃደኛ አልነበረም። አቤቱታ ለመስማት የፈቀደ አንድም ባለሥልጣን አልተገኘም። ሰልፈኛው በምክር ቤቱ በራፍ ላይ በነበረበት ጊዜ ባለሥልጣናቱ በስልክ እየተነጋገሩ የነበረው ከባህርዳር ፈጥኖ መድረስ ስለሚኖርበት ገዳይ ሠራዊት ብዛት ነበር። ሰልፈኛው ምላሽ ሲያጣ ለአቤቱታው ራሱ ውሳኔ ሰጠ - ሕዝባዊ ውሳኔ። እናም ሰልፈኛው በራሱ ውሳኔ ግንባታው ያጣድፈው ገባ። ገዳይ ሠራዊት ሌላ አገር ቢሆን ኖሮ ለጦርነት እንጂ በአድማ መበተኛነት ሥራ ላይ የማይውሉ መሣሪያዎችና ጥይቶች ታጥቆ ተላከና ደረሰ። ወደ ሰማይ፣ ወደ ግራ ወይም ወደ ቀኝ ሳይሆን በቀጥታ በሥራ ወደተጠመዱት ምዕመናን ተኮሰ። እናቶች፣ አባቶች፣ ወጣቶች ጮሁ፤ ሰሚ አልነበረም። አልሞ ተኳሾች ከሃያ በላይ የሚሆኑትን አነጣጥረው ጣሉ ከእነዚህም ሶስቱ ወዲያኑ ሕይወታቸው ሲያልፍ ሁለቱ ደግሞ ሆስፒታል ደርሰው ለዘላለሙ አሸለቡ፤ ቀሪዎቹ ለአካል ጉዳት ተዳርገው በስቃይ ላይ ይገኛሉ። እስቲ ይኸንን ውንብድና ምን ይሉታል?

ውድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ!!! የወያኔ መሰሪ መቅበጥበጥ የመጨረሻው ጣራ መድረሱን ልብ በል። አንዴ የመነኩሴዎችን ካባ እየለበሰ ነቢዩ መሐመድን በአደባበይ በመዘለፍ ሞስሊሞችን በክርስቲያኖች ላይ ያነሳሳል። ሌላ ጊዜ ደግሞ በደሴ እንደታየው ሞስሊሞች ስለተቃወሙ ለቤተክርስቲያን መሬት መስጠት አልቻልኩም ብሎ ክርስቲያኖችን በሞስሊሞች ላይ ያነሳሳል።

ለወያኔ ትንኮሳ የደሴ ሞስሊም ማኅበረሰብ በሰጠው «እኛ ተቃውመን አናውቅም ምላሽ» ወያኔ ምን ያህል እንዳፈረ መገመት ቀላል ነው። እንዲህ ዓይነት ዓይን ያወጡ ትንኮሳዎች በደሴም በሌሎችም ቦታዎችም መቀጠላቸው አይቀርም ምላሻችን እንደ ደሴ ሞስሊም ወንድሞቻችን «አንጣላልህም፤ ይልቁንስ የችግሮቻችን ምንጭ አንተ ነህና ወጊድ!» የሚል መሆን ይኖርበታል።

ይህንን ከፋፋይ ሥርዓት ለማስወገድ በኅብረት መነሳትን ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ አጣዳፊ ጉዳይ ነው። በሁሉም የአገራችን ሃይማኖቶች ተከታዮች ፍቅርና የኅብረት ትግል ወያኔን አስወግደን ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈነባት ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ቆርጠን እንነሳ።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

# ሃይለ ሀሳብ

## የህብረት ትግል ለምን? ዶር ብርሃኑ ነጋ (ካለፈው የቀጠለ)

### *የህብረት ትግል ሙከራዎች ያገጠሙት እክሎች ምን ነበሩ?*

ወያኔ ስልጣን ከያዘ በሁዋላ በኢህአፓ ግንባር ቀደምትነትና በመኢሶን ተባባሪነት በዳያስፖራና፣ ከሃገር በቀል ብሄርተኛ ፓርቲዎች ጋርም በመዳበል የተሞከሩ ብዙ የህብረት ጅምሮች ነበሩ ። እንደሚታወቀው ኢህአፓና መኢሶን አናርኪስትና ባንዳ ተባብለው በ1960ዎቹ መጨረሻ ላይ ደም የተቃቡ ድርጅቶች ነበሩ ። የዚህን የታሪካቸውን ቁርሾ ፣ መሪዎቹ ምን ያህል ቁጭ ብለው ተወያይተውና የጋራ መተማመን ላይ ደርሰው፤ ከዚህም ውይይት ጠንካራ የአመለካከትና የስነልቡና አንድነት ፈጥረው ሕብረቱን እንደፈጠሩ አላውቅም፡፡ እኔ ስገምተው ወያኔን ከስልጣን ለማሽቀንጠር ብቻ የተደረጉ ስምምነቶች ብቻ ስለነበሩ፣ በዚህም ምክንያት እርስ በእርስ የመጠባበቅ፣ ያለመተማመን፣ የመሻኮትና የመጠላለፍ ብሎም የመተማማት ችግሮችን በውስጡ አዝሎ የሚካሄድ ህብረት ስለነበር ይሆን እንዴ ዘላቂነት ያጣው የሚል ጥርጣሬ በብዙ ሰው አእምሮ ውስጥ ሳይቀረፅ አይቀርም እላለሁ፡፡ ቢያንስ ግን በኔ ግምት እንዲህ አይነት ታሪካዊ ጠባሳን ለአገራዊ ጉዳይ በሚል ተሻግሮ መሄዱ የሚያስመሰግነውን ያክል የታሪኩን ጉዳይ ቢያንስ መሪዎቹ ተነጋግረውበትና አንድ አይነት መግባባት ላይ ደርሰውበት፤ አባሎቻቸውንም አሳምነውበት ቢሆን ሕብረቱን ለማዝለቅ ይጠቅም ይሆን እንዴ የሚል ጥያቄ ይጭርብኛል፡፡ ትምህርት የምንቀስምበት ተመክሮ መሆኑም ይሰማኛል፡፡

ሌላው የግንቦት 97 ምርጫ ከመምጣቱ በፊት በሃገርቤት ውስጥ የተሞከረው የቅንጅት የተባበረ ትግል ነው ። በ1992 በተካሄዱት የከባቢና ፌዴራላዊ ምርጫዎች፣ ተቃዋሚዎች እርስ በርሳቸው ባይጠላለፉ ኖሮ ቢያንስ አዲስ አበባን ለማሸነፍ ይችሉ ነበር የሚል ግምገማ የነበራቸው ሰዎች ፣ በ1997ም ያ እንዳይደገም አንድ ነገር ማድረግ አለብን በሚል የቅንጅትን መፈጠር እውን እንዲሆን ማድረግ ችለው ነበር ። እንደታለመውም አራቱን ድርጅቶች በማስተባበር፣ ከአዲስ አበባም አልፎ በሃገር አቀፍ ደረጃም ምርጫውን ማሸነፍ የተቻለበትንም ሁኔታ መፍጠር ተችሎ ነበር። ያ ለውሱን አላማ፣ ምርጫውን ለማሸነፍ የተመሰረተ የትግል ህብረት ግን፣ ወደ ላቀ ሕብረት ለመመስረት ሲሸጋገርና፣ በወያኔ በኩል የሚመጣውን የተቀናበረ ጥቃት ለመመከት የሚያስችል የአመለካከትና የአመራር ጥንካሬ ከማዳበሩ በፊት ተጠቃ። አንድ ሆኖ መቀጠልም አልሆነለትም፡፡ ይብስ ብሎም ዋናውን ጠላቱን ትቶ ለረጅም ጊዜ የሚያሳፍር የእርስ በእርስ ንትርክ ውስጥ ገብቶ አረፈው፡፡ ይህ ክስተት ወደፊት ለሚያጋጥመን ሁኔታ ብዙ ሊያስተምረን የሚችል ትምህርት ይገኝበት ይሆናል ብዬ አስባለሁ ።

### *ከተሞከሩት የህብረት ትግሎች ምን እንማራለን?*

ዋነኛው ትምህርት የህብረቱን ግብ ግልፅ አድርጎ ማስቀመጥ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን መረዳት ይመስለኛል። የኢትዮጵያ አንድነትና ዴሞክራሲያዊ ሽግግር ግባችን ሊሆን ይገባል በሚል ግንቦት ሰባት ንቅናቄ በግልፅ ያስቀመጠው አላማ አለ። ይህንን ግብ አላማቸው ያደረጉ ህብረ ብሄራዊም ሆኑ ብሄራዊ ድርጅቶችን፣ በሃገር ቤቱ የትግል አውድማ ተጨባጭ ስራን የሚሰሩ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ፣ የህብረቱ አባል መሆን ይገባቸዋል እላለሁ። እነኝህ ሁለት አላማዎች ወሳኝ ናቸው ስንልና የሕብረቱ አባል ለመሆን አስፈላጊ ናቸው ስንል በጉዳዩ ዙሪያ ምንም ክርክር አይነሳም ለማለት አይደለም፡፡

የመጀመሪያውን ግብ በሚመለከት ነገሩን በጥርጣሬ የሚያዩና በተለይ የዴሞክራሲው ሙከራ እክል ቢገጥመው ‹ከኢትዮጵያ ውጭ ሰላምና ዴሞክራሲን ለመፈለግ እንዳንሞክር መንገዱ ከአሁኑ ለምን ይዘጋል? ‹የመገንጠል መብት መኖር በዴሞክራሲው ላይ መተማመን እስከሚፈጠር ድርስ ማስተማመኛ አይሆንም ወይ? ኢዴሞክራሲያዊው ወያኔ እንኩዋን ይህን መብት በሕገመንግስቱ ውስጥ አስገብቶት የለም ወይ እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ለምን ይፈሩታል? የሚሉ ጥያቄዎች በተለይ በዘውግ ከተደራጁ ድርጅቶች እንደሚነሳ አውቃለሁ፡፡ይህንን በሚመለከት ከሁለቱም ወገን ብዙ መከራከሪያዎች መቅረብ የሚችሉ ቢሆንም ፍርሀቱን ይቀርፍ እንደሆን ለጊዜው ሁለት መከራከሪያ ላቅርብ፡፡ የመጀመሪያው መከራከሪያ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታን አስቸጋሪነት የሚመለከት ነው፡፡ እንኩዋን በግማሽ ልብ ገብተንበት በሙሉ ልባችን ገብተንበትም ብዙ እክሎችን አልፈን የምንደርስበት ስርአት ነው፡፡ ከተመሰረተ በሁዋላ ጠንካራ የሆነውን ያክል በእንደኛ አይነት አገር ለመመስረት ቢያንስ በፖለቲካ ልሂቁ ዘንድ በግለሰቦች መሪዎች ወይንም ድርጅቶች ላይ ሳይሆን በጨዋታ ሕጉ ላይ ጠንካራና የማይዛነፍ ስምምነት ይፈልጋል፡፡ ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት የሚገነቡት በልሂቆች መሀከል ከፍተኛ የፖለቲካ ሽኩቻ ሲኖርና በጫወታው ሕግ ዙሪያ ግን የሽኩቻውን ያክል የጠነከረ ስምምነትና ታማኝነት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ ይህ የሚፈጠረው ደግሞ ጨዋታው ለሚካሄድበት የፖለቲካ ማህበረሰብ ጠንካራ ታማኝነት ሲኖር ነው፡፡ በምርጫ የተሸነፈ ወይንም የሚፈልገውን የፖለቲካ ስልጣን ያላገኛ ብሄረተኛ ነኝ ባይ ንኡስ ከበርቴ ሁሉ በፈለገ ጊዜ ጥቂት የሚጮሁ ተከታዮቹን ይዞ፤ የፖለቲካ ስርአቱን የሚያግትበት ሁኔታ የሚፈጠር ከሆነ እራሱን ከምር የሚወስድና ለጫወታው ህግ ክብር ያለው የዴሞክራሲ ስርአት ለመገንባት በፍፁም ከባድ ነው የሚሆነው፡፡ በሌላ በኩል ግን እስታሊናዊ የሆኑ የወያኔ አይነት መንግስቶች ይህንን አይነት ‹መብትን› ሕገ መንግስት ላይ ለመፃፍ የሚደፍሩትና በዚህም የበለጠ ዴሞክራቶች ነን ብለው የማያውቃቸውን ለማሞኘት የሚሞክሩት፤ የራሳቸውን ሕገ መንግስትም ከምር ስለማይወስዱት ነው፡፡ ለነሱ ሁሉም ነገር ጊዜያዊ የመግዢያ መሳሪያ ነው፡፡ ሕግ ራሱ የማጥቂያ መሳሪያ ነው፡፡ ለነሱ ሕግ ማለት የተፃፈውና ሁሉም የሚያውቀው ሳይሆን እነሱ የሚፈልጉትን ነገር የሚያደርጉበት ነው፡፡ የሚከበር ነገር የለም፡፡ ወያኔ የመገንጠል መብትን አይደለም (ምናልባት አስፈላጊ ከሆነ ለራሱ ሊጠቀምበት ሲፈልግ ካልሆነ በስተቀር) ፤ እንዲሁ እራስን በመረጡት የአካባቢ ሰው ለማስተዳደር የማይፈቅድ፤ በስም ደረጃ እራስን የማስተዳደር መብት ሰጥቶ ግን መሪዎቹን እሱ ለማስቀመጥ ምንም አይኑን የማያሽ፤ ከዚያም አልፎ ያንን ሕዝብ የሚወክለውን ድርጅት እሱ ራሱ ያስቀመጠው ካልሆነ ምንም የማያምን መንግስት መሆኑን፤ ይህ መስሎአቸው በአንድ ጊዜ ለሙከራም ቢሆን ተጠግተውት የነበሩት የዘውጌ ማህበረሰብ ድርጅቶች በሙሉ የሚያውቁት ነው፡፡ ማናቸውም መብቶች የሚከበሩት ለመብት ክብር ያለው ስርአት ሲኖር ነው፡፡ ለነኝህ መብቶች ከልቡ የሚቆረቆር አካል ከልቡ መስራት ያለበት የሰውን መብት ከልቡ የሚያከብር ስርአት ለማቆም፤ ይህን ስርአት ከልባቸው ለማቆም ከሚፈልጉ ሀይሎች ጋር ሆኖ መታገልና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ስርአትን በአገራችን መገንባት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የሚመጣ ምንም ጥቅም ወይንም የሚከበር ምንም መብት አይኖርም፡፡ ይህንን ከልባችን ስለምናምን ነው በጣም ግልፅ ሆነን ይህን ስርአት በዚህ የፖለቲካ ማህበረሰብ ውስጥ በጋራ ለመገንባት የቆረጡ ሀይሎች እንዲህ አይነቱን በመርህ ላይ የተመሰረተ ትብብር መመስረት አለባቸው የምንለው፡፡

ሌላው ከእስከ ዛሬዎቹ የህብረት ሙከራዎች የተማርነው፣ ህብረት ድርጅት ነኝ ያለ ሁሉ የሚገባበት ሳይሆን ድርጅት መሆኑን ከሚገልፀው ስሙና ፕሮግራሙ በላይ በተጨባጭ፤ በተግባር በትግሉ ሜዳ ላይ ለትግሉ አስተዋፅኦ ሊያደርጉ በሚችሉ፤ ትግሉን ከምር በሚወስዱ ሀይሎች መሀከል የሚፈጠር የምድር ላይ ግንባር መሆን አለበት፡፡ እራሴ የምመራውና እንደፈለግሁ የማደርገው ሶስት ሰው ያለበት ድርጅትም ቢሆን እመሰርታለሁ እንጂ በአላማ ከሚስማሙኝ ድርጅቶች ጋር ተቀላቅዬ እንዴት እሰራለሁ ብሎ የሚያምን ግብዝ ሁሉ፤ ወይንም ሌላው ኑሮ ሰልችቶኛል በማህበረሰቡ የሚያሳውቀኝ የፖለቲካ ሱቅ መክፈት አለብኝ ብሎ የሚያምን ሁሉ ፓርቲ መስርቼአለሁ እያለ፣ ራሱን እንቅልፍ ነስቶ ሌላውንም የሚያምስበት የፖለቲካ አካሄድ ሊቆም ይገባዋል ብለን እናምናለን። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እራሳችንን ከኛ ለተሻለ መሪ፤ ድርጅታችንን ከኛ ድርጅት ለላቀና ውጤት ለሚያመጣ ሰፊ ድርጅት፤ በግላችን አጠንክረን ከምናምንበት ግን ተግባራዊ ሊሆን ከማይችል እምነታችን ይልቅ ከሌሎች ጋር አስተሳስሮ ሊያታግሉን ለሚችሉ መለስተኛ እምነቶቻችን ለመልቀቅ በመርህ ደረጃ ፈቃደኛ ሳንሆን ከራሳችን በላይ ለሆነ ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ አላማ እንገዛለን ማለት ዘበት ነው፡፡ ለዚህም ነው፣ <<በሃገር ቤቱ የትግል አውድማ ተጨባጭ ስራን የሚሰሩ>> የሚል መመዘኛ ማስገባት አስፈላጊ የሆነው። ለትግሉ ከውጭ ሆነው አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚፈልጉ የተለያዩ ቡድኖች ወይንም ግለሰቦች ሊኖሩ አይገባም ለማለት አይደለም፡፡ ይገባልም ለትግሉም በጣም ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሚፈጠረው ግንባር ተጨባጭ የምድር ላይ ስራ እንዲሰራ ከሆነ የሚመሰረተው ግን ይህን ለማድረግ በተዘጋጁ ሀይሎች መሀል መሆኑ የግድ ነው፡፡ አባል ድርጅት አድርጎ ሊያቅፋቸው የሚገባውና ትክክልም የሚሆነው ይኸው ነው፡፡

የከዚህ በፊት ልምዳችን ይህን ማድረግ ያልቻለው በሁለት ምክንያት ይመስለኛል፡፡ አንደኛው የሚፈጠሩ ትብብሮችንና ተግባራዊ ግንባሮችን መለየት ላይ የሚፈጠር ብዥታ ይመስለኛል፡፡ የፖለቲካ ድርጅት ያልሆኑ (ለምሳሌ የሙያ ድርጅቶች፤ የሰብአዊ መብት ተሙዋጋች ቡድኖች...ወዘተ) ሁሉ የሚሰባሰቡበት በተወሰኑ ቁልፍ ጥያቄዎች ዙሪያ የሚደረግ አገራዊና በተወሰነ ደረጃም ጊዜያዊ ትብብር (ለምሳሌ ሰብአዊ መብት እንዲከበር፤ የታሰሩ የህሊና እስረኞች እንዲፈቱ...ወዘተ) ሊፈጠር ይችላል፡፡ ትክክልም ነው፡፡ ይህ ግን እኛ ከጠራነውና የጋራ ትግሉን ወጥ አመራር ሰጥቶና ሁለገብ ትግል አድርጎ እዳር ለማድረስ ከሚመሰረት ግንባር ጋር ይለያል፡፡ እኛ የጠራነው በምድር ላይ ሆነው ትግሉን ለማድረግ በወሰኑና ለዚህም በተደራጁ ሀይሎች መሀከል ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው፡፡ ይህ ማለት ከሌሎች በውጭ ብቻ ከተቋቋቁዋሙ ሀይሎች ጋር በተወሰኑ ስራዎች ላይ አይተባበርም ማለት አይደለም፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ግን የሚመስለው ዝም ብሎ ይሉኝታ ነው፡፡ የፖለቲካ ድርጅት ነኝ ያለ ሁሉ ለምን አይገባም፤ ይህ ማግለል ይመስላል፤ ጥቂት ግለሰቦችም ቢሆኑ እነሱን ከማስቀየም ዝም ብሎ ማስገባት ይሻላል፡ ካልገቡ ከዳር ሆነው ይበጠብጣሉ...ወዘተ በሚል የሚደረግ ሀቀኛ ያልሆነ የይሉኝታ አካሄድ ነው፡፡ የዚህ ችግር ደግሞ ቀድሞውንም በቅንነት ስላልተደረገ ብዙም ሳይቆይ ከዚሁ ጋር የተያያዘ ሀሜት አለመተማመንና አለመከባበር፤ ይፈጠርና ትብብሩን ይበክለዋል፤ ያዳክመዋል፡፡ ትግሉ የሚፈልገው ቆራጥነት ሳይኖር፤ በጋራ መስዋእትነት ለመክፈል በመፍቀድ ላይ የተሳሰረ መተማመን ከሌለ ደግሞ ዘላቂ ትብብር ወይንም ግንባር ሊመሰረት አይቻልም፡፡

ሶስተኛው ትምህርት፣ በወያኔ ባላንጣነት ላይ የማይደራደር የትግል ግንባር ሊሆን ይገባዋል። ከእንግዲህ ወያኔ የህዝብ ጎራን መቀላቀል የሚችለው፣ ራሱን ለዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተገዢ ለማድረግ ሲወስንና፣ ኢትዮጵያ የምትባል በአያቶቻችን መስዋእትነት የተገነባች ለሁላችንም እኩል የሆነች አንድ ሃገር መኖሯንና፣ አንድነቷም ለድርድር የማይቀርብ መሆኑን ወዶም ሆነ ተገዶ ሲቀበል ብቻ መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል። የሚፈጠረው ግንባር እንደዚሁ ጊዜያዊ ማስፈራሪያ ለመሆንና ጊዜ ጠብቆ በወያኔ ትናንሽ መደለያዎች እጁን ሰጥቶ ጠቅልሎ የሚገባ ሊሆን አይገባም፡፡ የዚህ አይነቱን ግንባር ከመፍጠር አለመፍጠሩ ይሻላል፡፡ ለዚህ ነው በመርህ ላይ የተመሰረተ፤ የሚሄድበትን የሚያውቅና ወጥ አመራር ያለው፤ እዚያም እንዴት እንደሚደርስ በደንብ ያሰበበትና እዚያ ለመድረስ በሚያስፈልገው እስትራቴጂም ላይ ሙሉ ስምምነት ያለው ትብብር መሆን የሚገባው፡፡

አራተኛው ትምህርት፣ አንዳንድ ጉዳዮች በይደር ቢቀመጡ፣ ዛሬ ትኩረት ልናደርግባቸው በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ እንድናተኩር ስለሚያደርገን፣ በሆነው ባልሆነው ከመናቆር ይጠብቀን ይመስለኛል ። ለሁሉም ችግሮች ዛሬ መልስ ሊኖረን አይገባም ። ሃገራችን ባለችበት ሁኔታ የሚያስፈልጋት፣ የተለያዩ ማህበረሰቦችን ጥቅም ወክለው የሚደራደሩ ፖለቲከኞችን ሳይሆን፣ "በየዋህነት ሽማ የተጋረዱ" (ጆን ሮውልስ ‹ቬይል አፍ ኢግኖራንስ›፤ የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ታሳቢ ያደርጋል) አርቆ አሳቢ ሃገር ወዳዶችን ነው ። የኦሮሞውን፣ የሙስሊሙን፣ የሴቶችን ወዘተ ጥቅም እንዴት ባለአቋም ላስከብር ብለው በሚያውጠነጥኑ ፖለቲከኞች ድርድር ሳይሆን፣ ዛሬ ሃገራችን ካለችበት መቀመቅ እንዴት ትውጣ፣ ለሁሉም ዜጎቿ ፍትሃዊ የሆነ ስርአት መሰረት እንዴት እንጣል የሚሉ አርቆ ተጨናቂዎች የተሰባሰቡበት የትግል ግንባር ቢሆን፣ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መስራች አባቶችና እናቶች ሽንጎ ጅማሮ ሊሆን ይችላል፣ ይገባልም ብዬ አስባለሁ ። አለበለዚያ ዝርዝር የፖለቲካ ፕሮግራሞችን ይዘን ለመደራደር ብንሞክር፣ "እርሷ መሬት የግል ይሁን ያለችው ገንዘብ ያላቸው ትግሬዎችና ጉራጌዎች ከደሃው ኦሮሞ ላይ ገዝተው ህዝባችንን መሬት አልባ ልታስደርግ አስባ መሆን አለበት" ወዘተ የሚል ተቃውሞና የማያልቅ ክርክር ስለሚጋብዝ፣ ዝርዝር የፖለቲካ፣ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ፕሮግራሞች፣ ከሽግግሩ ዘመን በሁዋላ ለሚደረግ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ መተው ያለበት ይመስለኛል። ስለቀሰምናቸው ትምህርቶች ይህን ካልኩ ዘንዳ፣ በመግቢያዬ እንዳልኩት በናንተም ተሳትፎ እንዲዳብር፣ ዝርዝር ውስጥ ከመግባት ልቆጠብና፣ ወደ ህብረቱ የመርህ መሰረቶች ላምራ።

**ይቀጥላል**

**የወያኔው አገዛዝ በአለም ላይ ካሉ 10 አፋኝ፣ ገዳይና አሸባሪ መንግስታት መካከል** (ከገጽ 1 የዞረ)

በተያያዘ ዜናም የአሜሪካ መንግስት በመለስ ዜናዊ አምባገንን አገዛዝ በመሰላቸት፣ አገዛዙ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስድ ማሳሰቢያ መስጠቱን የውስጥ ምንጮቻችን ተናግረዋል። ሰሞኑን የአሜሪካ መንግስት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ምክትል ሀላፊ፣ ኢትዮጵያን በጎበኙበት ወቅት፣ አምባገነኑ መለስ ዜናዊ የሰው ልጆችን መብት እንዲያከብር፣ ከኤርትራ ጋር ያለውን የድንበር ችግር እንዲፈታ፣ ጀግናዋን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ከእስር እንዲለቅና በአጠቃላይም በኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ለውጥ እንዲያመጣ ጠናካራ ትእዛዝ አስተላልፈዋል። የአሜሪካን ትእዛዝ በማስፈጸም ተወዳዳሪ የሌለውና ህልውናውን በአሜሪካ ሀይል ያቆየው የአሻንጉሊቱ መለስ ዜናዊ አገዛዝ፣ ከቀረበለት ጥብቅ ትእዛዞች መካከል የተወሰኑትን ይፈጽማል ተብሎ ይጠበቃል። በባድመ ከገባበት አዘቅት መውጣት የሚችለው ባድመን ለኤርትራ ሲሰጥ ብቻ በመሆኑና ይህንም ካደረገ የትግራይን ህዝብ ተቃውሞ እንደሚያስነሳበት የሚናገሩት አስተያየት ሰጪዎች፣ ዲሞክረሲያዊ ምርጫ ካደረገም እንደ 1997 ቱ ምርጫ ሁሉ ባሳፋሪ ሁኔታ ሽንፈት ስለሚከናነብ የአሜሪካው ባለስልጣን የሰጡትን ትእዛዛት ይፈጽማል ተብሎ አይታሰብም። ሁሉም ትእዛዞች የሚፈጸሙ ከሆነ የመለስና የአገዛዙ እድሜ ይቆረጣል የሚሉት ተንታኞች፣ ምናልባት ወ/ት ብርቱካንን በመፍታት ለአዲሱ አስተዳደር እጅ መንሻነት ለጠቀምበት ይችላል ብለዋል።

## የመለስ አገዛዝ የምሥራቅ አፍሪካ መረጋጋት ዋነኛ እንቅፋት መሆኑን አለም እየተረዳ (ከገጽ 1 የዞረ)

መለስ በተሳሳተ ና በተንሻፈፈ ስሌት “ሶማሊያ እንድንገባ ከተፈለገ ዓለማቀፉ ማህበረሰብ ከክብርና ሞገስ ጋር በግልፅ ሊለምነን ይገባል“ ማለቱን ተከትሎ የአሜሪካው የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍተኛ ባለስልጣን ጆኒ ካርሰን ለሮይተርስ በሰጡት መግለጫ “ኢትዮጵያ ወደ ሶማሊያ ዳግም እንዳትገባ” ማሣሰባቸው ”የሚሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ የሚለውን የአበው ብሂል የሚያስታውሰን ነው” ብለዋል የ ፖለቲካ ሳይንስ ምሁሩ።“ይህም የወያነ መንደሩ ዋነኛ ምሁር ፖለቲካዊ ዕውቀት ከዐለማቀፉ ማህበረሰብ እሳቤ ጋር ምን ያህል መራራቁን የሚያመለክት ነው ያሉት ምሁሩ ኢትዮጵያን ታህል ታላቅ አገር በባለሀሳቦች ሳይሆን በባለ ስሜቶች የምትገዛበት ጊዜ ላይ መድረሷ እጅግ አሳፋሪ ነው ብለዋል።

ይህም በተሳሳተ ፖሊሲ አለምን ሲያውክ የነበረው የቡሽ አስተዳደር በባራክ አባማ መተካቱን ተከትሎ የመለስ ዜናዊ አገዛዝም የምሥራቅ አፍሪቃ ሰላምና መረጋጋት ዋነኛ እንቅፋት መሆኑን አለም እየተረዳ መምጣቱን የሚያመላክት ታላቅ ፖለቲካዊ እርምጃ ነው ያሉት ምሁሩ፤ አለም ሀቁን ለመረዳት ቢዘገይም መዘግዬት ጨርሶ ከመቅረት ይሻላልና እርምጃው የሚደገፍ አቋም ነው ብለዋል።

ካርሰን እንዳሉት ኢትዮጵያ በራሷ ደህንነት ላይ አደጋ እንዳይፈጠር ድንበር ላይ ሆና የራሷን ግዛት የመጠበቅ መብቷን የሚያከብሩ ቢሆንም ከዚያ አልፎ ወደ ሶማሊያ ግዛት ውስጥ መግባቷን አገራቸው አሜሪካ አትደግፈውም። በመሆኑም ኢትዮጵያ ዳግም ወደ ሶማሊያ ጦሯን እንዳትልክ አሣስበዋል።

ከዚህም ባሻገር የባራክ አባማ አስተዳደር ከሳምንታት በፊት ለሶማሊያ የሽግግር መንግስት የሚያደርገውን ወታደራዊና ማቴርያላዊ ድጋፍ በኡጋንዳና በጅቡቲ መንግስታት በኩል ለማድረግ መወሰኑን ያስታወሱት ምሁሩ፤ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የሚያሳዩት “በሶማሊያ ጉዳይ ከኔ ወዲያ ፉጭት አፍ ማሞጥሞጥ ነው “ በሚል እሳቤ-“ ሳይጠሩት አቤት-ሳይልኩት ወዴት” ሲል የነበረው የመለስ አገዛዝ፤በዐለማቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ ታማኝነትና ተፈላጊነት ማጣቱን የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ሰዎች ያልሆነ መንቀዥቀዥ ሲያሳዩ አበው የሚሏት አንድ ስንኝ-የሶማሊያን ጉዳይ አስመልክቶ መለስ የደረሰበትን ሁለንተናዊ ኪሳራ የምትገልፀው ይመስለኛል”ያሉት ምሁሩ፤ ስንኟም፦”ተወደድኩኝ ብለሽ አትበይ ጠንገር ገተር

እኛም አንድ ሰኞ እንዲህ

አርጎን ነበር” የምትል ነች ብለዋል።

**የኢትዮጵያ ህዝብ ግንቦት 7 እያቀረበ ላለው ሁለገብ የድጋፍ ጥሪ የሚሰጠው ምላሽ አስደናቂ** (ከገጽ 1 የዞረ)

ግንቦት 7 በቅርቡ የወያኔን ሀይል በመረጠው ቋንቋ ለማነጋገር ዝግጅቱን በማጠናቀቅ ላይ መገኘቱ ሲታወቅ፣ አሁን ያለው የኢትዮጵያውያን ተሳትፎ ተጠናክሮ በቋሚነት ከቀጠለ፣ ወያኔን ከታሰበው ፍጥነት በላይ በሆነ ፍጥነት ድባቅ መምታት እንደሚቻል ታውቋል። የዛየሩ መሪ የነበረውን አምባገነኑን የሞቡቱ ሴሴሴኮ አገዛዝ ለማስወገድ የካቢላ ሀይል የወሰደበት ጊዜ የ7 ወር እድሜ ብቻ እንደነበር የሚያስታውሱት ታዛቢዎች፣ የወያኔው አገዛዝም ከሞቡቱ አገዛዝ ባልተናነሰ ደረጃ በስብሶ የሚገኝ በመሆኑ አገዛዙን ነቃቅሎ ለመጣል ረጅም ጊዜ እንደማይወስድ ተናግረዋል። የሞቡቱ አገዛዝ በሙስና የተዘፈቀ፣ በአንድ ጎሳ ሰዎች ይመራ የነበረና ከፍተኛ የሆነ የውጭ ድጋፍ ሲያገኝ የነበረ አገዛዝ መሆኑን ያስታወሱት አስተያየት ሰጪዎች፣ የመለስ አገዛዝም በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

የወያኔ የመከላከለያ ሀይል በውስጡ በዘር የተከፋፈለና በጥቂት የትግራይ ጄኔራሎች ቁጥጥር ስር የወደቀ በመሆኑ፣ አብዛኛው ወታደር ከዚህ እስራት አምልጦ ከኢትዮጵአ የትንሳኤ ልጆች ጋር በማበር የወያኔን መረብ እንደሚበጣጥስ ያላቸውን እምነት የገለጹልን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሲሆኑ፣ እነሱም በየትኛውም ቦታ ቢሆን ወያኔን ሄደው ለመፋለም ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

## በዘር ፍጅት የተከሰሰው ዘረኛው መለስ ዜናዊ የዘር ፍጅትን በማስቆም (ከገጽ 1 የዞረ)

በዋንኛነት በዘረ ማጥፋት የሚጠረጠሩ ከፍተኛ የቀድሞ የሩዋንዳን ባለስልጣኖችን ለሩዋንዳ አሳልፎ በመስጠቱ ነው።ወያኔ በህግ እና በስርአት የሚመራ ቢሆን ኖሮ ታንዛኒያ አሩሻ ላይ የዘረ ፍጅቱን ያስችል ለነበረው የተባበሩት መንግስታት ፍርድ ቤት የዘረ ፍጅት ተጠርጣሪዎችን አሳልፎ መስጠት ነበረበት ያሉት ታዛቢዎች አለምአቀፍ ህግን ተጻሮ ተጠርጣሪዎቹን በቀጥታ ለፓውል ካጋሜ መስጠቱ እንደትልቅ ውለታ ተቆጥሮለት ለሽልማት ሳያበቃው እንዳልቀረ ተናግረዋል።ኬኒያ እና ሌሎች ሀገራት፤ በሩዋንዳ የዘረ ፍጅት የፈጸሙትን የቀድሞ የሩዋንዳ ከፍተኛ ባለስልጣኖች፤የኢንተርሀውሜ ሚሊሻ ሀላፊዎችን እና በተለያዩ መንገዶች እልቂቱን የደገፉትን በአለምአቀፉ ህግ መሰረት የሩዋንዳ የዘረ ፍጅት ብቻ ለማስቻል በታንዛኒያ አሩሻ ተቋቁሞ ለነበረው የተባበሩት መንግስታት ፍርድ ቤት መስጠታቸው ይታወቃል።

መለስ ዜናዊ በተጨማሪ የዩጋንዳው ፕሬዚደንት ይዎሪ ሙሶቪ እና የቀድሞ የታንዛኒያ መሪ ጁሊየስ ኔሬሬ እንደተሸለሙ ተዘግቧል። ፍጽም አይን ባወጣው ዘረኝነቱ፤ጨፍጫፊነቱ እና ነፍሰገዳይነቱ የኢትዮድያ ህዝብ የሚያውቀው መለስ ዜናዊ በምንም አይነት መመዘኛ የዘረ ፍጅት ለማጥፋት ሚና ተጫውቷል ተብሎ መሸለም ባይገባውም በአፍሪካ መሪዎች እከክልኝ ልከክልህ ዘይቤ ዛሬ ተሸላሚ ቢሆንም ጊዜው ሲደርስ በአጋዴን፤በጋምቤላ፤በአዋሳ በፈጸማቸው የዘረ ፍጅቶች ከአለምአቀፍ ፍርድ ቤት መቅረቡ አያጠራጥርም ተብለአል።

**<u>ግጥም</u>**

ወያኔ፣ በ1987 አም ገደማ በአማራው ክልል ያደረገውን መሬት የማከፋፈል ስራ በተመለከተ ፣ በተለይም የኮር አባል እየተባሉ በሚጠሩት የወያኔ ካድሬዎች ላይ ባላገሩ የነበረውን ቅሬታ፣ በደርጉ ጊዜ ከነበረው ስርአት ጋር እያነጻጸረ እንዲህ ሲል ነበር የገለጸው፤

አስራት ቀረ ብየ አርፌ ስተኛ<br>
ኮታ ቀረ ብየ አረፌ ስተኛ<br>
የኮር አባል መጣ የባሰው ቀማኛ<br>
መሬቴን ወሰደው ሰፍሮ በመጫኛ

ጣሊያን አልመጣብን ተኩስ አልተተኮሰ<br>
ወይ ወራሪ አልመጣ ችግር አልደረሰ<br>
በኮር የተነሳ አገሩ ፈረሰ

ይታይህ ማቻከል ይሰማህ ጎዛምን<br>
ይታይህ በረንታ ይሰማህ ጥላት ግን<br>
እግዚዮ በል እነሴ ጎንቻና ሳር ምድር<br>
እግዚኦ በል አዋበል እግዚኦ በል አንደድ<br>
እንዴት ይወሰዳል መሬታችን በግድ

ሸማግሌ ጠፍቶ ገደብ ጊዮርጊስ ላይ<br>
ሰባት ሌቦች ሆነው አብረው በአንድ ላይ<br>
ነጭ ጤፍ እንዳፈር የሚዛቅበትን<br>
አስለኩት በገመድ አጽመ ርስታችንን

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**

**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

በ17870 KHZ በ 16 ሜትር ባንድ እና በ18350 KHZ በ19 ሜትር ባንድ ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

**ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን።** g7radio@ginbot7.org